

## የዮሐንስ እናት ኤልሳቤጥ

- ኤልሳቤጥ ከአሮን ዝርያ የተገኘች ናት። በዚያን ጊዜ በእስራኤል ውስጥ ካህን ለነበረ ለዘካርያስ ሚስቱ ነበረች። መፅሐፍ ቅዱስ ስለሁለቱ ባልና ሚስቶች ሲናገር፣ "በእግዚአብሔር ፊት ፃድቃን፣ ሁሉንም የእግዚአብሔርን ሕግጋትና ትዕዛዛት በመፈፀም ምንም ነቀፋ የሌለባቸው፣" ብሎ ይመሰክርላቸዋል። እርሷና ባሏ ምንም እንኳን ቢያረጁም ልጅ ግን አልወለዱም ነበር።

- አንድ ቀን ዘካሪያስ በቤተመቅደሱ ውስጥ እያገለገለ በነበረበት ወቅት መልአኩ ገብርኤል ተገለጠለት። በሚያየው ነገር ደነገጠ። ሆኖም መልአኩ መፍራት እንደሌለበት ነገረው። እግዚአብሔር ለእርሱ የሚሆን መልዕክት ነበረው። መልእክቱም ኤልሳቤጥ ልጅ ትወልዳለች የሚል ነበር! ለብዙ ዓመታት ሲፀልዩበት የነበረው የፀሎት ርዕስ ተመለሰላቸው። ዘካሪያስም ለሚወልዱት ልጃቸው የሚያወጣለት ስም ዮሐንስ እንደሆነ አውቋል።

- መልአኩም ሕፃኑ በእግዚአብሔር ፊት ሞገስ ያለው ነው አለ። ማንኛውንም ብርቱ መጠጥም ሆነ የወይን ጠጅ መጠጣት እንደሌለበት ነገረው። ይልቁንስ በመንፈስ ቅዱስ ይሞላል። ዋነኛ ተልእኮውም የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለጌታ ለኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ ማዘጋጀት ነው።

- ዘካሪያስ መልአኩ የሚነግረውን ነገር አላመነም። ካለማመኑም የተነሳ ሕፃኑ እስከሚወለድ ድረስ መናገር እንደማይችል መልአኩ ነገረው። ዱዳ ይሆናል።

- ከመቅደሱ ውጭ ያሉት ሰዎች ዘካሪያስ ስለቆየባቸው በጣም ተገርመዋል። በመጨረሻም ዘካሪያስ ከቤተመቅደስ ሲወጣ መናገር አይችልም ነበር። ስለዚህም ሲጠባበቁት የነበሩ ሁሉ ራዕይ እንዳየ ተረዱ።

- ልክ የእግዚአብሔር መልአክ እንደተናገረውም ኤልሳቤጥ ፀነሰች። ለአምስት ወራት ያህል ራሷን ደበቀች፤ የትም ቦታም አልሄደችም። አንድ ቀን እርሷን የምትጎበኝ ሴት መጣች። እርሷም ዘመዷ ማርያም ነች። እርሷም ብትሆን በመልአኩ ገብርኤል እንደተጎበኘችና የኢየሱስ ክርስቶስ እናት እንደምትሆን ተነግሯታል። ማርያም ገና ልጅ እንደፀነሰች ሳትነግራት ኤልሳቤጥ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልታ ነገሩን አወቀችው። እንዲህም አለቻት፣ “ከሴቶች ሁሉ ተለይተሽ የተባረክሽ ነሽ። የማህፀንሽም ፍሬ የተባረከ ነው።፡ ማርያምም እንዲህ ስትል ዘመረች፣

ነፍሴ ጌታን ታከብረዋለች፥<br>
መንፈሴም በአምላኬ በመድኃኒቴ ሐሴት ታደርጋለች፤<br>
የባሪያይቱን ውርደት ተመልክቶአልና። እነሆም፥<br>
ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል።

- ማሪያም ከኤልሳቤጥ ጋር ለሶስት ወራት ቆየች። ከዚያም ወደ ቤቷ ተመለሰች። አሁን ኤልሳቤጥ ልጅ የምትወልድበት ሰዓት ተቃርቧል። ልጇ በተወለድበት ጊዜ ወዳጆቿና ዘመዶቿ እጅግ ደስ አላቸው። ሁሉም ልክ እንደአባቱ የልጁ ስምም ዘካሪያስ ይሆናል ብለው አስበው ነበር። ኤልሳቤጥ ግን፣ “የልጁ ስም ዮሐንስ ነው፣” አለች።

- ዮሐንስ? ከዘመዶቻቸው መካከል በዚህ ስም የተጠራ ማንም የለም። ያለምንም ጥርጥር ኤልሳቤጥ ይህንን ስም በመምረጧ ተሳስታለች ብለው ተናገሩ። ዘካሪያስ መናገር ስለማይችል በምልክት ስለዚህ አሁን ለሕፃኑ ስላወጡለት ስም ጠየቁት። የሚፅፍበትን ነገር ጠየቃቸውና፣ “ስሙ ዮሐንስ መባል አለበት፣” ብሎ ማረጋገጫ ሰጣቸው። ወዲያውም ዲዳነቱ ቀረና መናገር ጀመረ። ከዚያም ስለሆነው ነገር ሁሉ እግዚአብሔርን ማመስገን ጀመረ። በዚያ የነበሩ ሰዎች ሁሉም፣ “ይህ ምን አይነት ልጅ ይሆን?” ብለው መገረም ጀመሩ። ዘካሪያስም፣ “አንተ ሕፃን የልዑል አምላክ ነቢይ ትባላለህ፤ ምክንያቱም በጌታ ፊት እየሄድክ መንገድን ታዘጋጃለህና፣” ብሎ ተነበየለት።

ኤልሳቤጥና ባሏም ልጁን አሳደጉት። እርሱም በመንፈሱ የጠነከረ ሆነ።

*ስለኤልሳቤጥ በሉቃስ ምዕራፍ 1 ላይ ማንበብ ትችላላችሁ።*

http://gardenofpraise.com